# 2ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች

፩ ጳውሎስና ስልዋኖስ ጢሞቴዎስም፥ በእግዚአብሔር
በአባታችን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስም ወደምትሆን ወደ
ተሰሎንቄ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን፤
፪ ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስም
ጸጋ ሰላምም ለእናንተ ይሁን።
፫ ወንድሞች ሆይ፥ እምነታችሁ እጅግ ስለሚያድግ
የሁላችሁም የእያንዳንዳችሁ ፍቅር እርስ በርሳችሁ ስለሚበዛ፥
ሁልጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን እንደሚገባ ልናመሰግን
ግድ አለብን፤
፬ ስለዚህ በምትታገሡበት በስደታችሁና በመከራችሁ ሁሉ
ከመጽናታችሁና ከእምነታችሁ የተነሣ በእግዚአብሔር አብያተ
ክርስቲያናት ስለ እናንተ ራሳችን እንመካለን።
፭ ስለ እርሱ ደግሞ መከራ ለምትቀበሉለት ለእግዚአብሔር
መንግሥት የምትበቁ ሆናችሁ ትቈጠሩ ዘንድ፥ ይህ
የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ ምልክት ነው።
፮-፲፪ እግዚአብሔርን የማያውቁትን፥ ለጌታችንም ለኢየሱስ
ክርስቶስ ወንጌል የማይታዘዙትን ይበቀላል፤

## ፪

፩-፫ ማንም በማናቸውም መንገድ አያስታችሁ፤ ክህደቱ
አስቀድሞ ሳይመጣና የዓመፅ ሰው እርሱም የጥፋት ልጅ
ሳይገለጥ፥ አይደርሰምና።
፬ እኔ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ አዋጅ እየነገረ በእግዚአብሔር
ቤተ መቅደስ እስኪቀመጥ ድረስ፥ አምላክ ከተባለው ሁሉ፥
ሰዎችም ከሚያመልኩት ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ ከፍ
የሚያደርገው ተቃዋሚ እርሱ ነው።
፭ ገና ከእናንተ ጋር ሳለሁ፥ ይህን እንዳልኋችሁ ትዝ
አይላችሁምን?
፮ በገዛ ራሱ ጊዜም ይገለጥ ዘንድ፥ የሚከለክለውን አሁን
ታውቃላችሁ።
፯ የዓመፅ ምሥጢር አሁን ይሠራልና፤ ብቻ ከመንገድ
እስኪወገድ ድረስ አሁን የሚከለክል አለ።

፰ በዚያም ጊዜ ጌታ ኢየሱስ በአፉ መንፈስ የሚያጠፋው፥
ሲመጣም በመገለጡ የሚሽረው ዓመፀኛ ይገለጣል፤
፱-፲፫ እኛ ግን፥ በጌታ የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ፥
ሁልጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን ልናመሰግን ግድ አለብን፥
እግዚአብሔር በመንፈስ መቀደስ እውነትንም በማመን ለመዳን
እንደ በኵራት መርጦአችኋልና፤
፲፬ ለዚህም የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር ለማግኘት
በወንጌላችን ጠራችሁ።
፲፭-፲፯ እንግዲያስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ጸንታችሁ ቁሙ፥
በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን የተማራችሁትን ወግ
ያዙ።

# ፫

፩-፫ ነገር ግን የሚያጸናችሁ ከክፉውም የሚጠብቃችሁ ጌታ
የታመነ ነው።
፬ የምናዛችሁንም አሁን እንድታደርጉ ወደ ፊትም ደግሞ
እንድታደርጉ ስለ እናንተ በጌታ ታምነናል።
፭ ጌታም ወደ እግዚአብሔር ፍቅር ወደ ክርስቶስም ትዕግሥት
ልባችንን ያቅናው።
፮ ወንድሞች ሆይ፥ ከእኛ እንደ ተቀበለው ወግ ሳይሆን ያለ
ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ
ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን።
፯ እኛን ልትመስሉ እንዴት እንደሚገባችሁ ራሳችሁ
ታውቃላችሁና፤ በእናንተ ዘንድ ያለ ሥርዓት አልሄድንምና፤
፰ ከእናንተ ዘንድ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት፥ ሌሊትና
ቀን በድካምና በጥረት እየሠራን እንኖር ነበር እንጂ፥ ከማንም
እንጀራን እንዲያው አልበላንም።
፱ ይህም እኛን ልትመስሉ ራሳችንን እንደ ምሳሌ እንሰጣችሁ
ዘንድ ነበር እንጂ፥ ያለ ሥልጣን ስለ ሆንን አይደለም።
፲ ደግሞ ከእናንተ ጋር ሳለን። ሊሠራ የማይወድ አይብላ
ብለን አዘናችሁ ነበርና።
፲፩ ሥራ ከቶ ሳይሠሩ፥ በሰው ነገር እየገቡ፥ ያለ ሥርዓት
ከእናንተ ዘንድ ስለሚሄዱ ስለ አንዳንዶች ሰምተናልና።
፲፪ እንደነዚህ ያሉትንም በጸጥታ እየሠሩ የገዛ እንጀራቸውን
ይበሉ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናዛቸዋለን
እንመክራቸውማለን።

፲፫ እናንተ ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ መልካም ሥራን ለመሥራት
አትታክቱ።
፲፬ በዚህ መልእክት ለተላከ ቃላችን የማይታዘዝ ማንም
ቢኖር፥ ይህን ተመልከቱት፥ ያፍርም ዘንድ ከእርሱ ጋር
አትተባበሩ።
፲፭ ነገር ግን እንደ ወንድም ገሥጹት እንጂ እንደ ጠላት
አትቍጠሩት።
፲፮ የሰላምም ጌታ ራሱ በሁሉ መንገድ ዘወትር ሰላምን
ይሰጣችሁ። ጌታ ከሁላችሁ ጋር ይሁን።
፲፯ በገዛ እጄ የተጻፈ የእኔ የጳውሎስ ሰላምታ ይህ ነው፤
የመልእክቴ ሁሉ ማስረጃ ይህ ነው፤ እንዲህ እጽፋለሁ።
፲፰ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን።

# መጽሐፍ ቅዱስ
# The New Testament in the Amharic language of Ethiopia

copyright © 1962, 2003 United Bible Societies

Language: አማርኛ (Amharic)

**Amharic NT**

Revised Amharic Bible in XML (2003).

Printed version by United Bible Societies (C)1962.

E-Text in transliterated ASCII format by Lapsley/Brooks Foundation 1994.

Unicode UTF-8 transformation and XML-tagging by Dirk Röckmann 2003 (www.nt-text.net).

With kind permission of the Bible Society of Ethiopia.

Every non-commercial work using this data in any form must fully include this copyright statement!

Every commercial use of parts or the complete data in any form needs written permission of the Bible Society of Ethiopia!

2014-09-09

---

PDF generated using Haiola and XeLaTeX on 18 Apr 2025 from source files dated 31 Aug 2023
2432e07d-4260-5d76-afcb-ce35bd1c48b7